የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ኤምባሲ
ኦታዋ
EMBASSY OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
OTTAWA

# የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲ በቶሮንቶ ከሚኖሩ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን ጋር ውይይት አካሄደ

በካናዳ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲ እ.ኤ.አ ማርች 29 ቀን 2014 በቶሮንቶ እና በአካባቢው ከሚገኙ የታላቁ ህዳሴ የህዝብ አስተባባሪ ም/ቤት አባላትና ከተለያዩ የኢትዮጵያ ኮሚኒቲ የተውጣጡ ተወካዮች ጋር ውይይት አካሄደ፡፡ በዕለቱ በተዘጋጀው የእራት ግብዣ ሥነ-ሥርዓት ላይ ክብርት አምባሳደር ብርቱካን አያኖ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ባለሙሉ ስልጣን አምባሣደርና ልዩ መልዕክተኛ በመገኘት ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ከተውጣጡ የኮሚኒቲ ተወካዮች፣ የሀይማኖት አባቶች፣ ወጣቶች፣ ሴቶች እንዲሁም የቶሮንቶና የኪችነር የታላቁ ህዳሴ ግድብ አስተባባሪ የህዝብ ተሳትፎ ም/ቤቶች ጋር ትውውቅና በወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ዙሪያ መግለጫ ሰጥተዋል፡፡ አምባሳደር ብርቱካን በተለይ የታላቁ የህዳሴ ግድብ ሦስተኛ ዓመትን አስመልክቶ በዕለቱ ለተሰበሰቡ ኢትዮጵያዊያንና ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በሠቱት መግለጫ፤ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ በካናዳ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያንና ትውልድ ኢትዮጵያዊያን በተለያዩ የህዳሴ ም/ቤቶች ራሳቸውን በማደራጀት ቦንድ በመግዛትና የነፃ ድጋፍ በመስጠት እስካሁን ድረስ ላበረከቱት አስተዋጾ ያላቸውን አድናቆትና ምስጋና በማቅረብ በቀጣይም የግድቡ ሥራ እስኪጠናቀቅ ድጋፋቸውን አጠናክረው እንዲንቀሳቀሱ

ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡ የስብሰባው ተካፋዮችና የህዳሴ ም/ቤት አስተባባሪዎች ለታላቁ ህዳሴ ግድብ መጠናቀቅ የተቻላቸውን ሁሉ ድጋፍ እንደሚሠጡ ቃል የገቡ ሲሆን፤ ሃገራዊ ልማትና ብልፅግናን ለማምጣት በሚደረገው ትግል ሁሉ የበኩላቸውን ለመወጣት ዝግጁነታቸውን ዳግም አረጋግጠዋል፡፡ የህዝብ ተሳትፎ አስተባባሪ ም/ቤቶች እ.ኤ.አ በ2014 የሚያካሂዱትን የገቢ ማሰባሰቢያ ዝርዝር ፕሮግራም ለተሣታፊዎች ይፋ አድርገዋል፡፡ በዕለቱ የህዳሴ ግድብ 3ኛ ዓመት ምክንያት በማድረግ የተሠጡ መግለጫዎች፣ ሪፖርቶችና ቀስቃሽ ሙዚቃ ለተሳታፊዎች ቀርቧል፡፡

በቶሮንቶ በተካሄደው ስብሰባ ከ130 የማያንሱ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተወካዮች፣ የሀይማኖት አባቶች እንዲሁም ከታዋቂ አርቲስቶች መካከል ዝነኛው አርቲስት አሊ ቢራ በሥነ-ሥርዓቱ ተካፍለዋል፡፡ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲ በኦታዋ ተመሣሣይ ትውውቅና በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት ያካሄደ መሆኑ የሚታወስ ሲሆን፣ በቀጣይም በተለያዩ የካናዳ ከተሞች ተመሣሣይ መድረኮች የሚያዘጋጅ መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለመግለፅ ይወዳል፡፡

ማርች 29 ቀን 2014/ መጋቢት 20 ቀን 2006 ዓ.ም

ኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ኤምባሲ

<u>ኦታዋ</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲ ኦታዋ
Embassy of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Ottawa